የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፫
አዲስ አበባ የካቲት ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6[th] Year No. 23
ADDIS ABABA - 10[th] February, 2000

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፭/፲፱፻፺፪ ዓ·ም·
የኢትዮ – ኩባ የኢኮኖሚ ፡ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምም ነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ............................ገጽ ፩ሺ፪፻፵፮

## CONTENTS

Proclamation No. 195/2000
Ethio-Cuba Economic, Scientific and Technical Co-Operation Agreement Ratification Proclamation ............................................Page 1246

### አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፭/፲፱፻፺፪

### የኢትዮ – ኩባ የኢኮኖሚ ፡ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና በኩባ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የኢኮኖሚ ፡ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት መስከረም ፫ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም አዲስ አበባ ከተማ ላይ የተፈረመ ስለሆነ፡

ስምምነቱ የሚጸናውና በሥራ ላይ የሚውለው ሁለቱ ወገኖች ከፈረሙበትና በየሕገ–መንግሥታቸው መሠረት አስፈላጊው ሥርዓት ሲሟላ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ ፡

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የኢትዮ – ኩባ የኢኮኖሚ ፡ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፭/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩባ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል መስከረም ፫ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም· አዲስ አበባ ላይ የተፈረመው የኢኮኖሚ ፡ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት በዚህ አዋጅ ጸድቋል።

### PROCLAMATION No. 195/2000

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE ETHIO–CUBA ECONOMIC, SCIENTIFIC AND TECHNICAL CO-OPERATION AGREEMENT

WHEREAS, an Agreement on Economic, Scientific and Technical Cooperation between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Cuba was signed at Addis Ababa, Ethiopia, on the 14[th] day of September, 1999;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force upon the fulfillment of their respective constitutional requirements following the signing of the Agreement by both parties;

WHEREAS, the House of Peoples Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 7[th] day of March, 2000;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "Ethio-Cuba Economic, Scientific and Technical Cooperation Agreement Ratification Proclamation No. 195/2000,"

2. *Ratification of the Agreement*

   The Agreement on Economic, Scientific and Technical Cooperation between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Cuba signed in Addis Ababa on the 14[th] day of September, 1999, is ratified.

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

3· *የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ሥልጣን*

የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

4· *አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ*

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



3. *Power of the Minister of Economic Development and Cooperation*

The Minister of Economic Development and Cooperation is hereby empowered to implement the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 7th day of March, 2000.

Done at Addis Ababa, this 7th day of March, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE